# ሠ ቅ ጸ ሰ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፡ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ ዕትም፲ | ጥር ፳፮ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ የፀና አቋም ወያዝ ማለት ምን ማለት ነው?

## ለድርድርም አይቀርብም ሲባል ምን ለማለት ታስቦ ነው?

በቅርቡ ኅልውናውን ይፋ ያደረገው፣የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በፕሮግራሙ ላይ የኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ የፀና አቋም አለው፤ በዚህ ጉዳይ ለድርድር አይቀርብም የሚል የጠነከ አቋም እንዳለው ገልጿል። ይህ ሲባል ምን ማለት ነው? የሚሉ ሀሳቦች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሲሰነዘሩ ይደመጣሉ። ሀሳቦቹን ግልጽ ማድረግም ተገቢ በመሆኑ እንደሚከተለው ይብራራል።

ዛሬ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሕዝቦች፣ የትም ይኑሩ የት፣ የኛ ብለው ተመልሰው የሚገቡበት መግቢያ ሀገር አላቸው። እነዚህ ሀገሮች እንደየ ታሪካቸው ሕዝቦቹ የተራመዱባቸው የወል ዕሴቶች ባለቤቶች እንዲሆን አድርጓቸዋል። በመሆኑም እነዚህን የጋራ ዕድድገታቸው ውጤቶች የሆኑትን ዕሴቶቻቸውን እንደ ዓይን ብሌኖቻቸው የሚጠበቁ የኅልውና ቅርሶቻቸው ናቸው ። የሁሉም ቤቶቻቸው ናቸው። እነዚህም ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ፣ትውልዱ ከወሪሪ ጠላት እየተከላከለና እየጠበቀ ለተከታዩ ትውልድ ሲያወርስና፣ተረካቢው ትውልድም በተራው ያን ሀገርን ጠብቆ ለተከታዩ ትውልድ የማስተላለፍን አደራ ተግባራዊ ሲያደርግ የመጣ እንደሆነ የኅብረሰብ ዕድገት ታሪካ ያሳያል። ይህ የሰው ልጅ ታሪክ ነው።

ኢትዮጵያ በዓለም ካሉት ሀገሮች አንዷ እንደመሆኗ፣ ሕዝቧ ለአንድነትና ሉዐላዊነት መጠበቅ በጽናት በመቆም ፣ የከፈለውና በመክፈል ላይ ያለው መስዋዕትነት እሱነቱን የሚገለጥበት ልዩ መገለጫው ሆኗል። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ሕዝብና እንደ ሀገር፣በዚች ሡፌ ምድር ላይ ከተሰባሰበበት የታሪክ ጊዜ ጀምሮ፣ እስካለንበት ወቅት ድርስ ታላቁን የታሪካችንን ድርሻ የሚይዘው አንድነትንና ሉዐላዊነትን ለመጠበቅ የተደረገው የተጋድሎና በዚህም የተመዘገቡት አኩሪ ድሎች፣ ሀገራችንን ከሌሎች ልዩ ያደርጋታል።

ለኢትዮጵያውያን የሀገር ሉዐላዊነትንና ሕዝቡን አንድነት ማስጠበቅ የነፃነትን ዋጋ ከመረዳት አልሆ ልዩ የባሕሪ መገለጫ ነው። በታሪካችን ከያንዳንዱ ትውልድ፣ ከያንዳንዱ መንደርና ከያንዳንዱ ቤተሰብ ለነዚህ ሁለት ማለትም አንድነትና ሉዓላዊነት ለተሰኙ ፣ የማይነጣጠሉ መለዮዎቻችን ለማስጠበቅና ለማስከበር ሲባል እልፈ አእላፍ ሕይዎት ተገብሯል። በመሆኑም ለሕዝቡ አንድነቱንና ሉዐላዊነቱን መጠበቅ የመኖር ወይም ያለመኖር ምርጫ አድርጎ የሚቆጥረውና እንደ ምህላ የተወሰደ ቅርስ ነው። ድርጅታችን የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የዚያ ቅርስ ተረካቢ፣የዛሬው የዐማራ ትውልድ ተጠሪ አድርጎ የቀረበ ድርጅት ነው። ድርጅታችን ይህንን ዐማራውም ሆነ ሌላው በኢትዮጵያዊነት የሚያምነው ትውልድ፣ ከአበው የተረከብነውን ሉዐላዊነትንና አንድነትን የመጠበቅ ኃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ ተከታዩ ትውልድ በሉዐላዊነትና ሕዝቡ አንድነት መጠበቅና መረጋገጥ ዙሪያ ብርቱ የፀና አቋም እንዲኖረው የማድረግን ኃላፊነትን ይገነዘባል። በአቻ ድርጅቶችም ዘንድ፣ እነዚህ መርሆቻች ላይ የማይናወጥ አቋም የመያዛቸው ጉዳይ፣ የማንነታቸው መገለጫ ነው ብለን እናምናለን። እንደዚህ ዓይነት አቋም ካላቸው ድርጅቶችም ጋር ሊኖሩ የሚገቡ ግኑኝነቶቻችን የሚገዛበት መርሕ ለአንድነታችንና ለሉዓላዊነታችን ከሚኖራቸው ትክክለኛ አቋም የሚመነጭ ነው ። በማንኛውም ግኑኝነቶቻችንና ትብብሮቻችን የሀገሪቱ ሉዐላዊነትና የሕዝቡ አንድነት ለድርድር የሚቀርቡ አይሆኑም። ለድርጅታችን እነዚህ መርሆዎች የማይነኩና አይደረሴዎች የሆኑ የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄዎች ናቸው።

በርግጥ፣ ከዚህ የገዘፈ የተጋድሎ ታሪክ ጎን ለጎንም አገራችንና ሕዝባችን የክሕደት ታሪክንም ያስተናገደች ሀገርና ሕዝብ ነን። በመሆኑም በታሪካችን በተከታታይ ለመጡ ወራሪዎች እና ቅኝ ገዥዎች መንገድ አመልካችና ተዋጊ ባንዳ በመሆን አገራቸውንና ወገናቸውን የወጉ የውስጥ ከሀዲዎች ሚና ከፍተኛ እንደነበር የተጋድሎና የነፃነታ ታሪካችን ያሳያል። ይህ ታሪክም ለኛው ትውልድ እንደ መጥፎ ቅርስ ከወላጅ ወደ ተወላጅ ሀገራችን ዛሬ ለምትገኝበት ምስቅልቅል ሁኔታ የዳረገን እንደሆነ ሕዝባችን እየገፋ ያለው መራር ሕይዎት በግልጽ ያሳል። ይህን በትግሬ-ወያኔ መራሽነት የደረሰን የመበታተን አደጋ ለመቋቋም፣ በመደረግ ላይ ያለው ተጋድሎና ሕዝቡ ለአንድነቱ እያደረገ ያለው ትግልና እየከፈለ ያለው መስዋዕትነት እናት ሀገራችን ከወደቀችበት ለማንሳት የሚደረግ ትግል ነው። ለትግሉ የሚከፈለው ሁለንተናዊ መስዋዕትነት፤ ልንከፍለውና መክፈልም ያለብን ከአበው በምሃላ የተረከብነው አደራ እንደሆነም በአጽንዖት እንገነዘባለን።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ኅብረት አንድነቷንና ሉዓላዊነቷን ታረጋግጣለች!

ውድ እናት ሀገር ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!